# በአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ

## በስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ የአምስተኛ ክፍል የተቀናጀ ሳይንስ ወርክሽት/መለማመጃ ጥያቄዎች

ሐምሌ፣ 2012 ዓ.ም

ባህር ዳር፣

## ምዕራፍ አራት

### 4.1 እንስሳት

**ማስታወሻ፡-**

- እንስሳት ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ዘአካለት ሲሆኑ ደንደሴና ኢ-ደንደሴ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡
- ደንደሴዎች ባለ አከርካሪ ( የጀርባ ) አጥንት ያላቸው ሲሆን፡- ለምሳሌ፡- አሳ ፣ እንቁራሪት ፣ አዕዋፍ ፣ ሰው…..ወዘተ
- ኢ-ደንደሴዎች ደግሞ የጀርባ አጥንት የሌላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ቢራቢሮ ፣ ዝንብ፣ ንብ ፣ አንበጣ …..ወዘተ

**ጥያቄዎች**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ደንደሴ እንስሳት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. እባብ ለ. የሃር ትል ሐ. አዞ መ. ጉርጥ ሠ. ሐና መ

2. እንስሳት እንዴት ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ?

   ሀ. በመራመድ ለ. በመሳብ ሐ. በመዋኘት መ. በመብረር ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. ከኢ-ደንደሴ እንስሳት የማይመደባው የትኛው ነው?

   ሀ. እባብ ለ. አባጨጓሬ ሐ. የወባ ትንኝ መ. ምስጥ

4. እንስሳት እንዴት እንደሚራቡ ግለፅ/ጭ?----------------------------------------------------------
5. እንስሳት የት ቦታ እንደሚኖሩ ጥቀስ/ሽ?---------------------------------------------------------

### 5.2 ሦስት አጽቂዎች

**ማስታወሻ፡-**

- ሦስት አፅቂዎች ከኢ-ደንደሴ የሚመደቡ እንስሳት ናቸው፡፡
- ሦስት አፅቂዎች እንደ ስማቸው ከ ሶስት የተከፈለ የአካል ክፍል አላቸው፡፡ ይኸውም ራስ ፣ እምቢያ እና ህልፅ ( ሆድ) ይባላሉ፡፡ እነዚህ የአካል ክፍሎች የየራሳቸው ተግባራት አሏቸው፡፡
- ሶስት አፅቂዎች ጥቅምም ፡ ጉዳትም አላቸው፡፡

**ጥያቄዎች**

6. የሦስት አፅቂዎች እግሮቻቸውና ክንፎቻቸው የተያያዙበት የአካል ክፍል የቱ ነው?

   ሀ. ራስ ለ. እምቢያ ሐ. ህልፅ መ. መልስ የለም

7. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛ ቅደም ተከተል የያዘ ሙሉ ልውጠተ ቅርፅ የቱ ነው?

ሀ. እንቁላል- ሙሽሬ- እጪ- ጉልምስ

ለ. እንቁላል- እጪ- ጉልምስ- ሙሽሬ

ሐ. እንቁላል -እጪ- ሙሽሬ- ጉልምስ

መ. እንቁላል-ጉልምስ-እጪ- ሙሽሬ

8. ከሚከተሉት ሶስት አፅቂዎች ጠቃሚ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የሐር ትል ለ. ጉንዳን ሐ. ዝንብ መ. አንበጣ

9. መንቀሳቀስ የማይችል ያለምግብ ለብዙ ጊዜ መቆየት ሚችል የሶስት አፅቄ የልውጠት ቅርፅ ደረጃ ማን ነው? ሀ. እንቁላል ለ. እጭ ሐ. ሙሽሬ መ. ጉልምስ

10. ከሚከተሉት ሶስት አፅቂዎች ውስጥ ከፊል ልውጠተ ቅርፅ የሚያሳየው የትኛው ነው?

ሀ. ዝንብ ለ. አንበጣ ሐ. የሀር ትል መ. ንብ

11. በዑደተ ህይወታቸው ውስጥ ልውጠተ ቅርፅ የማያሣይ እንስሳ የትኛው ነው?

ሀ. አንበጣ ለ. እባብ ሐ. ዝንብ መ. ንብ

12.የአንበጣን መንጋ ለመከላከል የሚያስችለን ዘዴ የትኛው ነው?

ሀ. ኬሚካልን በመርጨት ለ. ቆርቆሮ በማንኳኳት ሐ. ጅራፍ በማጮህ መ. ሁሉም

13.የሃር ትል ዑደተ - ህይወትን በቅደም ተከተል አስቀመጥ/ጭ?

______________________________________________

14.የሃር ትሎች የሀር ክርን የሚያመነጩት በየትኛው ዑደተ ህይወት ደረጃ ነው?

______________________________________________

## 4.3 ዓሣዎች

<u>ማስታወሻ</u>: **ዓሣዎች፡-**

- ደንደሴ እንስሳት ውስጥ ይመደባሉ፡፡
- በውኃ ውስጥ የሚኖሩና የሚራቡ ናቸው፡፡ ትንንሽ አሳዎችን፣ ሦስት አፅቂዎችን፣እንቁራሪቶችን እና በውሃ ውስጥ የሚገኙ ተክሎችን ይመገባሉ፡፡
- በሳንባቸው ይተነፍሳሉ፡፡

**<u>ጥያቄዎች</u>**

15. ዓሣዎች ምን አይነት ፅንሰት ያካሂዳሉ?

ሀ. ውስጣዊ ለ. ውጫዊ ሐ. ውስጣዊና ውጫዊ መ. መልስ የለም

16. ዓሣዎች የሚኖሩት በሀይቅ የውኃ አካል ብቻ ነው? ሀ. እውነት ለ. ሀሰት

17. ዓሳዎች እንዴት ይራባሉ?----------------------------------------------------------

18. ዓሣዎች ለምን ይጠቅማሉ?----------------------------------------------------------

19. የዓሣ ዝርያዎች እንዳይጠፉ ምን መደረግ አለበት?------------------------------------

## 4.4 እንቁራሪት አስተኔዎች

<u>ማስታወሻ</u>: **እንቁራሪት አስተኔዎች፡-**

- በየብስና በውኃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ናቸው፡፡ ከደንደሴ እንስሳት ይመደባሉ፡፡
- በውጫዊ ፅንስት በውኃ ውስጥ ይራባሉ፡፡ እንደሚኖሩበት ቦታ በስንጥባቸው ፣ በእርጥብ ቆዳቸው እና በሳንባቸው ይተነፍሳሉ፡፡

**<u>ጥያቄዎች</u>**

20. የእንቁራሪት አስተኔዎች ውስጣዊ የአካል ክፍል የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. አፍ ለ. አይን ሐ. እግር መ. ስንጥብ

21. የእንቁራሪት አስተኔዎች የመንቀሳቀሻ አካል የሆነው ?

    ሀ. አይን ለ. ቆዳ ሐ. እግር መ. ራስ

22. ለመራባት የግድ ውሃ የሚያስፈልጋቸው እንስሳት የትኞቹ ናቸው ?

    ሀ. ኤሊዎች ለ. እንቁራሪቶች ሐ. እባብ መ. አዞ

## 4.5 ገበሎ አስተኔዎች

<u>ማስታወሻ</u>: **ገበሎ አስተኔዎች፡-**

- ከደንደሴ እንስሳት ይመደባሉ፡፡ በመራመድ ፣ በመሳብና በመዋኘት ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡
- በየብስና በውሃ የሚኖሩ ደም ቀዝቃዛ እንስሳት ናቸው፡፡
- በሳንባቸው የሚተነፍሱ ናቸው፡፡ ምሳሌ፡- እባብ ፣ እንሽላሊት ፣ አዞ ፣ ኤሊ….ወዘተ

**<u>ጥያቄዎች</u>**

23. ገበሎ አስተኔዎች የሚራቡት በውሃ ውስጥ ነው?

    ሀ. እውነት ለ. ሀሰት

24. የገበሎ አስተኔዎች ፅንሠት የሆነው?

    ሀ. ውጫዊ ለ. ውስጣዊ ሐ. ውስጣዊና ውጫዊ መ. መልስ የለም

25. ዓሳና ገበሎ አሰተኔዎች በዑደተ-ህይወታቸው ውስጥ ልውጠት ቅርፅ ይታይባቸዋል?

ሀ. እውነት ለ. ሀሰት

## ምዕራፍ አምስት

## 5.1 ሰውነታችን

<u>ማስታወሻ:</u> ሰውነታችን፡-

- ሕይወት ያላቸው ዘአካላት ሁሉ በአካላቸው ውስጥ የተለያዩ ስነህይወታዊ ሂደቶችን ያከናውናሉ፡፡
  ምሳሌ፡- ከምግብ ሀይልን የመፍጠር ሂደት ( ህዋሳዊ ትንፋስ) ፣ አየር ማስገባትና ማስወጣት ፣ ያልተፈጨ ምግብን ከሰውነት የማስወጣት ሂደት ( ፅዳጂ ) ..ወዘተ

**<u>ጥያቄዎች</u>**

26. የፅዳጂ አባል አካል ክፍል ያልሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ሳንባ ለ. ኩላሊት ሐ. ልብ መ. ቆዳ

27. ካርበን ክለተ ኦክሳይድ የተባለውን የተቃጠለ አየር ማሰውገጃ አባል አካል የቱ ነው?

    ሀ. ኩላሊት ለ. ሳንባ ሐ. ከርስ መ. ቆዳ

28. ሁለቱ የግራና የቅኝ ኩላሊቶች ከሽንት ማጠራቀሚያ ፊኛ ጋር የሚገናኙት በምንድን ነው?

    ሀ. ቦየ ሽንት ለ. ቦየ ፊኛ ሐ. ሽንት ፊኛ

29. በቆዳ አማካኝነት የሚወገድ ፅዳጂ

    ሀ. ሽንት ለ. አይነምደር ሐ. የተቃጠለ አየር መ. ላበት

30. የቆዳ ተግባራት ከሆኑት ውስጥ ሶስቱን ጥቀሱ ?------------------------------------------------

    ---------------------------------------------------------------------------------------------------------

ትዕዛዝ ፡- በ ‘’ሀ” ስር ለተዘረዘሩት በ ‘’ለ” ስር ከተዘረዘሩት በመምረጥ አዛምዱ

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 31.የተጠራ ደም ከኩላሊት የወሰዳል | ሀ. ኩላሊታዊ ደም ወሳጂ |
| 32.ሽንትን ከሽንት ፊኛ ለማስወገድ ያገለግላ | ለ. ሽንት ፊኛ |
| 33.ያልተጣራ ደም ወደ ኩላሊት ይወሰዳል | ሐ. ቦዮ ሽንት |
| 34.ሽንትን ያጠራቅማል | መ. ኩላሊታዊ ደም መላሽ |

## 5.2 ምግብ

ማስታወሻ: **ምግብ :-**

- በሰውነታችን ውስጥ በኦክስጂን እየተቃጠለ ጉልበት በማመንጨት ለተለያዩ ተግባራት ለማከናወን እንጠቀምበታለን፡፡

**ጥያቄዎች**

35. ምግብ በሰውነታችን ውስጥ በኦክስጂን ተቃጥሎ የሚገኘው ውጤት ምንድን ነው?

ሀ. ጉልበት ለ. ካርበንክለተ ኦክሳይድ ሐ. ውኃ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

36. ምግብ ሳይበላሽ የማቆያ ዘዴ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በማድረቅ ለ. በማቀዝቀዝ ሐ. በጨው ማሻት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

37. ግለት ከሞቃት አካል ወደ ቀዝቃዛ አካል የሚተላለፍበት መንገድ የቱ ነው?

ሀ. በንክኪ ለ. በፍልክልክ ሐ. በጨረር መ. በሁሉም

38.ግለት በቁስ አልባ የመተላለፍ ዘዴ የሆነው ----------ነው?

ሀ. ጨረር ለ. ንክኪ ሐ. ፍልክልክታ መ መልስ የለም

39. ምግብን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ ሶስቱን ጥቀስ/ሽ ?---------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

40. ሶስቱን የመጠነ ሙቀት መለኪያ እርከኖች ዘርዝሩ ? ------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 5.3 የምግብ እጥረት

ማስታወሻ: **የምግብ እጥረት ዋነኛ መንስኤዎች:-**

- ድርቅ ፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ምርቱን በማርገፍ ፣ ከፍተኛ የተፈጥሩ ሀብት መመናመን የዝናብ እጥበትና ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ መከሰት ፣ የሚገኘውን የዝናብና የወንዝ ውኃ በአግባቡ አለመጠቀም የምግብ እጥረት መንስዔዎች ናቸው፡፡

**ጥያቄዎች**

41. የምግብ እጥረትን ለመቅረፍ ከሚያገለግሉ ዘዴዎች የሚመደባው-----------ነው?

ሀ.ውኃንማቆር ለ. የከረሰ ምድር ውኃን መጠቀም ሐ. ደን መትከል መ. ሁሉም መልስ ናቸው

42.በአካባቢያችን ችግኝ በመትከል የምናገኘውን ጥቅም ቢያንስ አራቱን ጥቀስ/ሽ?---------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

43. የወንዝ ውኃ ለምን አገልግሎት /ጥቅም እንደሚውል ዘርዝር/ሪ? ------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 5.4 ጎጂ ልማዶች

<u>ማስታወሻ፡</u> **ጎጂ ልማዶች ፡-**

- ቆሻሻን በአግባቡ አለማስወገድ (በየቦታው መጸዳዳት)፣ ጥሬ ስጋን መመገብ፣ ንጽህናው ያልተጠበቀ ውኃ መጠቀም ከጎጂ ልማዶች የሚመደቡና በሰው ጤና ላይ ችግር የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

**<u>ጥያቄዎች</u>**

44. የኮሶ በሽታ መንስኤው ምንድን ነው?  ሀ.ጥሬ ስጋ መመገብ ለ. የተበከለ ውኃ መጠጣት
    ሐ. ያልበሰሉ ፍራፍሬዎችን መመገብ  መ. ሁሉም መልስ ናቸው
45. ከሚከተሉት ውስጥ ውኃ ወለድ በሽታ የሆነው የቱ ነው?
    ሀ. ኮሌራ ለ. አሜባ ሐ. ብልሀርዚያ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## 5.5 ኤች አይቪ/ ኤድስ

<u>ማስታወሻ፡</u> **ኤች አይቪ/ ኤድስ ፡-**

- በዓለማችን ገዳይ በሽታና መድሃኒት ያልተገኘለት አንዱ ተላላፊ በሽታ ነው፡፡ ዋነኛ መተላለፊያ መንገዶቹም ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት፣ ስለታማ ነገሮችን በጋራ መጠቀም ፣ ያልተመረመረ ደም በመለገስ ፣ከእናት ወደ ልጅ በፅንስ አማካኝነት ፣ ጡት በማጥባት ወዘተ ናቸው፡፡
- ዋነኛ መከላከያ መንገዶች አራቱ የ "መ" ህጎችን መከተል ነው፡፡ እንሱም መታቀብ ፣መወሰን ፣መጠቀምና መመርመር ናቸው፡፡

**<u>ጥያቄዎች</u>**

46. የኤች አይቪ/ ኤድስ በሽታ መንስኤ የሆነው -------ነው?
    ሀ.ባክቴሪያ ለ. ፕላዝሞዲየም ሐ. ቫይረስ መ. ፈንገስ

# ምዕራፍ ስድስት

## 6.1 መሬት

<u>ማስታወሻ</u>: **መሬት ፦**

- በሥርዓተ ፀሐይ ውስጥ ትገኛለች። ሥርዓተ ፀሐይ በውስጡ ፀሐይና በፀሐይ ዙሪያ የሚዞሩ አካላትን ማለትም ፕላኔቶችን አካቶ የያዘ ሥርዓት ነው።አስትሮያድና ጅራታም ኮከብ (ኮሜት) የስርዓተ ፀሐይ አካል አይደሉም። ፕላኔቶች በግዝፈት ከፀሐይ ያነሱ ናቸው። ፕላኔቶች በራሳቸው ዛቢያ ላይ ያሽከረክራሉ። ፕላኔቶች እንደ ፀሐይ የራሳቸውን ብርሃን አያመነጩም።

<u>ጥያቄዎች</u>

47. ከሚከተሉት ውስጥ በስርዓተ ፀሐይ ውስጥ የሚካተት የቱ ነው?

ሀ. አስትሮይድ ለ. ኮሜቶች ሐ. ጅራተም ኮከብ መ. ፕላኔቶች

ትዕዛዝ ፦ በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት በ "ለ" ስር ከተዘረዘሩት በመምረጥ አዛምዱ

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 48. ለፀሐይ በጣም ቅርብ የሆነ ፕላኔት | ሀ. ሳተርን |
| 49. ከፀሐይ በጣም እርቆ የሚገኝ ፕላኔት | ለ. ጁፒተር |
| 50. ብዙ ጨረቃ ያለው ፕላኔት | ሐ. አንድ |
| 51. የመሬት የጨረቃ ብዛት | መ. ሜሪኩሪ |
| | ሠ. ኔፕቲውን |
| | ረ. ሁለት |

## 6.2 የስርዓተ ፀሐይ ክፍሎች

<u>ማስታወሻ</u>: **የስርዓተ ፀሐይ ክፍሎች ፦**

- ፀሐይ ትልቋ ኮከብ ነች። ኮከቦች ሞቃት ሉል ጋዝ ሆነው እርስ በርሳቸው በስርዓተ ቁሳዊ ሀይል የተያያዙ ናቸው። አብዛኛው የፀሐይ አካል የተገነባው ሰባ አምስት በመቶ ሃይድሮጅንና ሃያ አምስት በመቶ ሂሊየም ጋዝ ነው። ውስጠኛው ጋዝ እና በሌሎች ንብብሮች የተሸፈነው ክፍል የፀሐይ እምብርት (ቡጥ) ተብሎ ይጠራል።

<u>ጥያቄዎች</u>

52. በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ አሁን ላይ ባለው የስነ ፈለግ(አስትሮኖሚ) ጥናት ስንት ፕላኔቶች አሉ? ሀ. 9 ለ. 11 ሐ. 8 መ. 12

53. ምንም አይነት ጨረቃ የሌላት ፕላኔት ማን ናት?

ሀ. መሬት ለ. ሜሪኩሪ ሐ. ቬኑስ መ. ለ እና ሐ

54. ቀይ ፕላኔት በመበል የምትጠራው ፕላኔት ማን ናት?

ሀ. ማርስ ለ. መሬት ሐ. ቬኑስ መ. ጁፒተር

## 6.3. የመሬት እንቅስቃሴ

ማስታወሻ:

- መሬት ሁለት ዓይነት እንቅስቃሴዎች አሏት፡፡ እነሱም በራሱ ዛቢያ ላይ የምታደረገው መሽከርከርና በፀሐይ ዙሪያ መዞር ናቸው፡፡

**ጥያቄዎች**

55. መሬት በፀሐይ ዙሪያ ለመዞር ምን ያህል ጊዜ ይፈጅባታል?

ሀ. 365 ¼ ቀን ለ. አንድ ዓመት ሐ. 24 ስዓት ብቻ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

56. በፀሐይና በመሬት መካከል ያለው እርቀት በኪ.ሜ ስንት ነው?---------------------------

56. መሬት በራሷ ዛቢያ ላይ በመሽከርከር ሊፈጠሩ የሚችሉ ሦስት ሂደቶችን ጥቀሱ?-----------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

57. መሬት በራሷ ዛቢያ በ24 ሰዓት ከየት ወደ የት ትሽከረከራለች?

ሀ. ከምራብ ወደ ምስራቅ ለ. ከምስራቅ ወደ ምዕራብ

ሐ. ከሰሜን ወደ ደቡብ መ. ከደቡብ ወደ ሰሜን

58. አራቱን ዋና ዋና ወቅቶች ዘርዝሩ?-----------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

## 6.4 ግርዶሽ

ማስታወሻ: ግርዶሽ ፡-

- አንድ የጠፈር አካል በሌላው ላይ ጥላውን ሲጥል የሚከሰተው ሁኔታ ግርዶሽ ይባላል፡፡ ሁለት ዓይነት ግርዶሽ አሉ፡፡ እነሱም የጨረቃ ግርዶሽና የፀሐይ ግርዶሽ ይባላሉ፡፡
- የጨረቃ ግርዶሽ የሚፈጠረው የመሬት ጥላ በጨረቃ ላይ ሲወድቅ ነው፡፡ ይህ ማላት መሬት በፀሐይና በጨረቃ መካከል ስትሆን ነው፡፡
- የፀሐይ ግርዶሽ የሚፈጠረው የጨረቃ ጥላ በመሬት ላይ ሲያርፍ ነው፡፡ ይህ ማላት ጨረቃ በመሬትና በፀሐይ መካካል ስትሆን ነው፡፡

**ጥያቄዎች**

59. በ 2012 ዓ.ም የታየው ግርዶሽ መቼ ወር እና ቀን ተከሰተ?------------------------በአማራ ክልል ግርዶሹ የተከበረበት እና በአግባቡ የታየበት ከተማ ማን ይባላል?--------------------------

## 6.5 ሳተላይቶች

<u>ማስታወሻ:</u> **ሳተላይቶች:-**

- በአንድ ትልቅ አካል ዙሪያ የሚዞር ሌላ አካል ሳተላይት ይባላል ። ለምሳሌ :- ጨረቃ በመሬት ዙሪያ ትዞራለች በመሆኑም ጨረቃ የመሬት ተፈጥሮ ሳተላይት ናት። ሳተላይቶች የፀሐይን ብርሃን ወደ ኤሌክትሪክ ጉልበት በመቀየር እየተጠቀሙ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሬት ያቀርባሉ ። የተለያዩ የሳተላይት አይነቶም አሉ።

**<u>ጥያቄዎች</u>**

60. ሳተላይቶች በመሬት ላይ ለሚከናወኑ ተግባራት የሚሰጡት ጠቀሜታ የቱ ነው ?

ሀ. የአየር ንብረትን ለመቆጣጠር ለ. የቴሌፎን ግንኙነት ለመቆጣጠር

ሐ. የትምህርትና የህክምና አገልግሎትን ለመቆጣጠር መ. ሁሉም መልስ ናቸው

61. ለመርከቦች ጉዞና ለአውሮፕላን በረራ አቅጣጫን የሚያሳይ ሳተላይት የቱ ነው?

ሀ. የግንኙነት ሳተላይት ለ. መሪ ሳተላይት ሐ. የአየር ንብረት ዘጋቢ ሳተላይት

መ. የስርዓተ ፀሐይና ጠፈር ዘጋቢ ሳተላይት

62. ስለ ስርዓተ ፀሐየውና ስለህዋ አካላት መረጃ የሚሰበስቡ የሳተላይት አይነቶች ?

ሀ. የአየር ንብረት ዘጋቢ ሳተላይቶች ለ. የስርዓተ ፀሐይና ጠፈር ሳተላይቶች ሐ. መሪ ሳተላይቶች መ. መልስ የለም

63. ኢትዩጲያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመጠቀቻት ሳተላይት ስም እና ጥቅሟን ግለጽ/ጭ?-----------

64. በአሁኑ ስዓት በአለም አቀፍ በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፈውን የኮሮና ቫይረስ ወይም ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከል ተመራጭ ዘዴ የቱ ነው?

ሀ. ከአካላዊ ንክኪ መቆጠብ ለ. እጃችን በሳሙና መታጠብ ሐ. አፍን እና አፍጫን በማስክ መሸፈን መ ርቀትን መጠበቅ ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው